# እርቅ ወይንስ ፍትህ

ከበልጅግ አሊ

አቶ መርሻ ዮሴፍ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር በአንድ የፓልቶክ ከፍል ውስጥ ተገኝተው ብዙ ሰዓት የወሰደ ገለፃ ሰጥተዋል። ገለፃው ያተኮረው በአሁኑ ጊዜ የኢሕአፓ ጠላቶቸቹ በውሸት ፕሮፖጋንዳ ድርጅቱን ለማጥላላት የሚያነሱዎቸውን ጥያቄዎች እንደገና በማንሳት እውነቱን ለታዳሚዎቹ ለማቅረብ ጥረት አድርገዋል። ወይይቱ በጣም የተሳካ ነበር ማለት እችላለሁ ። ከጌታቸው ማሩ አሟማት እስከ ህብረት ጥያቄ ተነስተው ግልፅ የሆነ ውይይት ነበር የተደረገው። የድርጅቱን ልማትም ሆነ ጥፋትን በትክክል ለማስቀመጥ ያደረጉትን ጥረት ሳላደንቀው አላልፍም።

አንድ ጥያቄ ግን አሁንም ቢሆን በትክክል መልስ የተገኘለት አይመስለኝም። ስለ ቀይ ሽብርና  ስለ መኢሶን ጋር የተፈጠረው ሕብረትን በሚመለከት የተነሳው ጥያቄ ከባድነቱን እራሳቸውም አምነው፣ ነገር ግን እናት ሃገራችንን ለማዳን በወቅቱ ሕብረትን መፍጠር አስፈላጊ ነበር ብለው አጠቃለውታል።በዚህ ልስማማ ብችል እንኳ ግን ግልፅ ያልሆነልኝ ነገር ቢኖር ከኢሰፓ ጋር ያለው ሁኔታ ነው።

በአጠቃላላይ ሁኔታውን ብቀበለው በተግባር አተረጓጎም ላይ ግን ያለውን ሁኔታ እንደገና በዚህ ፅሁፌ ላነሳው ተገድጃለሁ። እዚህ ላይ ትልቅ የአተረጓጎም ስህተት ሊፈጥር እድሚችል ይሰማኛል።በኔ አመለካከት ከመኢሶን ጋር እርቅ ተደረገ  ማለት ከኢሰፓ ጋር ተደረገ ማለት አደለም።እንዲያውም የኢሰፓ አባላት ጥፋቱን ለኢሕአፓና ለመኢሶን ሰጥተው እራሳቸውን ነፃ ሲያደረጉ እናያለን።

በአሁኑ ወቀት ኢሰፓን ወክሎ ጥፋቱንም ሆነ ልማቱን የሚቀበል የለም።ሊቀመንበሩ መንግሰቱ እንኳን ሳይቀር ትንኝ እንኳን አልገደልኩም እያለ ጥፋቱን ወደ ሌላ ሲያስተላልፍ ነው የምንሰማው። የወያኔም ፍርድ ቤት እድሜ ልክ እስራት መንግስቱ ላይ ሲወስን ከእሱ በታች ለአሉት የሞትን ፍርድ ሰጥተዋል። የወያኔ ፍርድ በህፃንነታችን የተማርነው የፍርደ ገምድል ዳኛ ታሪክ ፍርድ አይነት ሁኖ ነው ያገኘሁት።

የነመንግስቱን ጉዳይ በተከላካይነት የያዘው ሆዳም ጠበቃ ባንዳ ሞላ ዘገዬና ባንዳው ሙልጌታ አስራተ በሪፖርተር ላይ ቃለ መጠይቅ አድርገዋል።ጠበቃው እራሱ በሰጠው ቃለመጠይቅ የመላኩ ተፈራ ጓደኛና በደርግ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበረው ሲሆን ከወያኔ የተሰጠው ስራ የደርግ ባለስልጣናት ስለ ቀይሽብር የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ለመጠየቅ መለስ  መድረክ እንዲያዘጋጅላቸው እንዲጠይቁ ማግባባት ሲሆን ያንንም እንደመከላከያ ነጥብ አቀረብኩ ነው የሚለው።እነዛም ጓደኞቹ ለመለስ በፅሁፍ ይቅርታ እንደጠየቁ ባንዳው ሙሉጌታ አስራተ በሌላው ቃለመጠይቅ ተናግሮአል።

ወያኔ ከቀይ ሽብር እኩል የኢህአፓን አባላት እንደጨፈጨፈ የሚታወቅ ሲሆን ወያኔን ማን ይቅር ባይ፣ ማንስ መድረክ አዘጋጅ እንዳደረገው  ባንዶቹን እጠይቃለሁ። ወያኔ ዛሬም ቢሆን የኢሕአፓን አባለት የት እንዳደረሰ አላስታወቀም መግደልም አላቆረጠም።ጠበቃውም ሆነ ወያኔ ተጠያቂ እንጂ መሀሪ አደሉም፣ መድረክ አዘጋጅም መሆን አይችሉም።

ሌላዎ ቃለመጠይቅ የሰጡት ወ\ት ሳባ አበርሃ „ደርግ አፈናና ጭፍጨፋ ሰብአዊ መብት ሊግ“ ውስጥ ዋና ፀሀፊ በቀጥታም ባይሆን  ወያኔ በዚህ ጉዳይ የህዝብ ድጋፍ እንዳላገኘ ገልፀዋል።ህብረተሰቡ መሰዋትነት መክፈል አይፈልግም ብለው ነው የተናገሩት።ሕብረተሰቡ ይህንን በግልፅ እንደሚያውቀው ለእሳቸው አይታያቸው እንጂ ለኛ ግልፅ ነው።መስዋትነትን መክፈል የለመደ ሕዝብ ዛሬ መፍራት ጀመረ ማለት አይችልም። ብዙ ልጆቻቸው በፋሽሽቶች የተገደሉባቸው ወላጆች ፍትህን ቢፈልጉም ከወያኔ ግን አይጠብቁም።

በቀይ ሽብር የተገደሉት በብዛት የኢሕአፓ አባላት ይሁኑ እንጂ ሌሎችም ተገድለዋል። ቀይ ሽብር መቼ ተጀምሮ መቼ አቆመ ብሎ መናገር የሚችል የለም ብዬ አምናለሁ ። ለኔ አሁንም ቀይ ሽብር እንዳለ ነው። ችግሩ አብሮን የሚጓዝ እንዳለን ሊዘነጋ አይገባም። የሚወዱዋቸው ልጆቻቸውን ያጡ ወይም አካላችን የተጎዳብን ሰዎች በፖለቲከኞች መካከል የሚደረገው እርቅ ብዙም ላይገባን ይችላል። ፍትህ እንጂ እርቅ ሁኔታውን አያስተካክለውም ። ከፍትህ በኋላ ምህረት ግን ይቻላል።ለዛውም በዳይ መበደሉን ሲያምን ነው። በዳይ ግን ትንንሽ ምክንያት  እየፈለገ ጥፈቱን ወደ ሚኞች ለመላከክ ጥረት እየተደረገ ባለበት ወቅት የቱ ላይ እርቁ እንደሚሰራ ሊገባኝ አልቻለም። ይቅርታስ ከመለስ ቢያገኙ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚቀበላቸው ይመስላቸዋል። ይህ ከድጡ ወደ ማጡ ነው የሚሆንባቸው።

በወያኔ ቁጥጥር ስር ያልሆኑት ከፍተኛ የደርግ ባለስልጣናት በውስጥ ተደብቀው በፀረ ወያኔ ትግል ውስጥ በሚስጥር ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ግለሰቦች ሊሆኑ አይገባም።ባለፉት ሳምንታት አንድ ቅንጅትን የሚደግፍ የፓል ቶክ ክፍል ካሳ ከበደን አቅርቦ ነበር። ይህ ደግሞ ቅንጀት የኢሰፓ ቅጣይ ነው ለሚለው የምዕራብ ጋዜጠኛ አሉባልታ (የቢቢሲን ሃርድ ቶክ ዝግጀትና ለአቶ ሃይሉ ሻውል የቀረበ ጥያቄ እናስታውስ) ሙሉ ትጥቅ እንደሰጠነውና እንዳሳመነው ግልፅ ነበር።

እነዚህ የደርግ ባለስልጣንኖች በመጀመሪያ እርዳታቸውን ከመስጠጣቸው በፊት ተቃዋሚዎችን ቃል የሚስገቧቸው ጉዳይ ቢኖር አንድ ነው። ፀረ ኢሕአፓ ሆነው መገኘትን ነው።የድርጅቱ መኖር እንቅልፍ ይነሳቸዋል ። ያጠፉት ሕይወት ያባንናቸዋል።ማንም ይሁን ማን ፀረ ኢሕአፓ ከሆን ይደግፉታል ። ልደቱን ወያኔ መሆኑን እያወቁ ፀረ ኢህአፓ አድርገው አብረው ደንሰዋል ።ዛሬ ደግሞ ድሮ ጠላታችን ከሚሉት ሻብያ ጋር ሆነው ኢሕአፓን ቁም ስቅሉን ያሳዩታል።ሃገራችንን ከማዳን በፊት ኢሰፓን ማዳን ከሚሉ ወገኖች ጋር ምን አይነት እርቅስ ህብረትስ ይቻላል?ዛሬ በፀረ ወያኔ ትግል ወስጥ የጅምላ ትግል እየተደረገ ነው። ይህ ደግሞ የተቃዎሚው ክፍል ለወያኔ እኛኑ የሚደበድብበት ዱላ እያቀበልን ነው የምንገኘው።ከሃገራችን በፊት ኢሰፓን እናድን በሚለው መፈክራቸው ሽንጣቸውን ገትረው ይታገላሉ። ስለ ገንዘብ እንጂ ሰላህገራቸው ምንም ፍቅር እንደሌላቸው በፈላሻዎች ላይ ያደረጉትን ልናስታውስ ይገባል።የለንደኑስ ድርድር እንዴት እንደነበር እንዘነጋዋለን እንዴ። ኢሕአፓ ወያኔን ለመዋጋት ኢደሃቅን ለማቆቆም በሚራወጥበት ጊዜ ካሳ ከበደ ፈላሻዎችን ሲሸጥ እንደነበር እንዘነጋዎለን።ለኔ ትላንትን መርሳት ዛሬን ትክክል አያደርገውም።

ከሀገራችን በተሰረቀው ገንዘብ ፀረ ወያኔ የሆነውን ትግል ለመቆጣጠር በካሳ ከበደና በሻብያ ጭፍረኞች የሚደረገው እንቅስቃሴ ካልቆመ በስተቀር ለወያኔ እኛኑ የሚቀጠቅጥበት ዱላ ከማቀበል አንቆጠብም።መንግሰቱም ሆነ ካሳ ከበደ ገንዘባቸውን በመጠቀም ወደ ስልጣን መመለስ እንደማይቻል ሊያውቁት ይገባል።የኢሰፓ አባላት ይቅርታ የሚጠይቁት ከልባቸው የኢትዮጵያን ህዝብ እንጂ የወያኔን ጠቅላይ ሚኒስተር

መሆን አልነበረበትም ። ሆዳሙ ሞላ ዘገዬ በየወያኔ ጋዜጣና ፓልቶክ እየሄደ ቢጨፍር የራሱን ሆድ ከመሙላት በስተቀር የሚያመጣው ሌላ ቁም ነገር የለውም።

ችግሩ ግን የኢትዮጵያ ህዝብ በችግሩ ግዜ ጥሎት የፈረጠጠውን አይረሳም። ሻብያና ወያኔ በተጠናከሩበት ግዜ የሃገሪቱን ብርቅ ጀነራሎች ከውጭ መንግስታት ጋር በመተባበር ያስጨረሰው ካሳ ከበደን የመሰሉ ሰዎች ጋር እንዴት እርቅ እንደሚደረግ አይገባኝም።እኔ በበኩሌ ፍትህና እርቅ አብረው ካልሄዱ ውጤት የለውም ባይ ነኝ።ለእያንዳንዱ በተናጠል ፍትህ ስጠይቅ ባጠቃለይ ግን እርቅን እደግፋለሁ። የጅምላ እርቅ ግን አይሰራም።ካሳ ከበደ ለሃገሩ ታሰበ እሱ ዛሬ በትግሉ ውስጥ መታየት የሚመጣውን ጉዳት አጥቶት አደለም ግን ከሃገሬ በፊት እራሴን ላድን በሚል እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል የሚለው የሆደሞች መፈክርን በመከተል ይመስለኛል እንዲህ ሲሮጥ የሚታየው።ካሳ ከበደ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ መጠየቅ ከፈለገ የተቃዋሚ ድርጅቶች ጋዜጦችና ራዲዮኖች ክፍት ናቸው። በተግባርም ጥላቻን ሳይሆን አንድነትን ሊሰብክ ይገባው ነበር።ነገር ግን ይህንን አደለም አሁን የምናየው። ከወያኔና ከሻቢያ ጋር በማበር ኢሕአፓን ለማጥፋት የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው።

ዛሬም ነገም መለስን ይቅርታ ለመጠየቅ የሚደረገው እሩጫ አገራችንን መልሶ መላልሶ እንደ መሸጥ ይቆጠራል። ባንዳ ሞላ ዘገየም ሆነ ሌሎች የኢሰፓ ባለስልጣናት ለሆዳቸው ሲሉ አገራችንን ለወያኔና ለሻብያ እንደገና ለመሸጥ መዘጋጀታቸው በታሪክ የሚያሰወቅስ ነው።

የኔ ምክር ለደርግ ባለስለጣናት በተለይም በእሰር ቤት ውስጥ ለማይገኙት ለኢትዮጲያን ህዝብ ከዚሁ ይቅርታ ቢጠይቁ የፀረ ወያኔን ትግል በጣም ያጠናክሩት እንደነበር ልገልፅ እወዳለሁ።ሌላ የምለቸው ቢኖር አንድ ግዜ ከአድርባይነት፣ከሆዳምነት፣ ከፋሽሽትነት፣ ከዘረኝነት፣ የነፃን ሕይዎት ሞክሩት።የኢትዮጲያን ሕዝብ ይቅርታ በመጠየቅ ልባችሁን አንፁ። አልጠራጠርም በልባችሁ ውስጥ የምታገኑት ንፁህነት ከገንዘብ የበለጠ ድስታን ይሰጣችኋል።

ኢሕአፓ አባላት ለነበርነውና አሁንም ለሆኑት ይህ የንፁህነት ደስታ ከማንኛውም የሚበልጥብን ስለሆነ እናንተም እንድትቀምሱት የዘወትር ፀሎታችን ነው።

ስለ እኛ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !!!

በልጂግ አሊ